# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**መስከረም 5 ቀን 2005 ዓ.ም.**

**በክፍፍል የተወጠረው የወያኔ ቡድን ጄኔራል መኮንኖችን ሾመ፤**

**ሹመቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ በፕሬዝዳንቱ ቢሮ አልታወቀም ተባለ፤**

**ወያኔ ድንገተኛ አስቸኳዋይ ስብሰባ አደረገ፤**

**ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የኢሕአዴግ ሊቀ መንበር ሆኖ ተሾመ**

**ደመቀ መኮንን ምክትል ሆን**

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተፈጠረው ችግር ስር እየሰደደ መጥቶ ባለስልጣናት ሚና ለይተው እርስ በርስ እየተፋለሙ ባለበት በዚህ ጊዜ ድንገት ሳይታሰብ ያለ አንዳች በቂ ጥናት የከፍተኛ መኮንኖች የማዕረግ እድገት ተሰጠ፡፡

34 ኮሎኔሎች የብርጋዲየር ጄኔራል ማዕረግ ሲሰጣቸው 3 ብርጋዴየር ጄኔራሎች ደግሞ የሜጀር ጄኔራል ማዕረግ እንደተሰጣቸው የታወቀ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዙት ከበረሃ የመጡ የህወሀት አባላት መሆናቸውም ታውቆዋል፡፡

በህወሀት ቡድን ውስጥ የታቀደ አንድ ምስጢር አለ ተብሎ ሲነገር ከነበረው መሀከል መኮንኖቹን ቦታ ቦታ ማስያዝ አንዱ እንደሆነ የጠቆሙት የውስጥ አዋቂ ምንጮቹ በተለይ የመኮንኖቹ መሾም በስብሀት ነጋ አደራጅነት የተጀመረው ስራ ተጠናክሮ እየገፋ መምጣቱን የሚያሳይ መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልጸዋል፡፡

የጄኔራሎች የማዕረግ እድገት ሲሰጥ የነበረው እስከዛሬ ድረስ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ በኩል እንደነበር የጠቆሙት ምንጮቹ ዛሬ አንዴ ከጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ሌላ ግዜ ደግሞ ከፕሬዝዳንት ቢሮ ወጣ በሚል ግልጽ ባልሆነ መልኩ ሹመቱ መሰጠቱ ግራ ያጋባ ጉዳይ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ኃይለማርያም ደሳለኝ የመለስን ቦታ እንዳይይዝ ከፍተኛ ጥረት እያደረጉ ያሉት ህወሀቶች የወያኔ ምክር ቤት ከመጀመሩ ጥቂት ቀናት አስቀድሞ ድንገት የማዕረግ እድገት እንዲሰጣቸው መደረጉ ህውሀቶች ወሳኝ የሆኑ ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው የተደረገ መሆኑን ምንጮቹ ገልፀዋል::

ማንም ሆነ ማንም ከህወሀት ውጭ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ቢይዝ እንኩዋን በሌላ ዘዴ ተጠቅሞ መልሶ ቦታውን መቆጣጠር የሚል ምስጢራዊ መመሪያ በማውጣት እየተንቀሳቀሱ ያሉት እነ ስብሀት ነጋ ካወጡት ምስጢራዊ ስልት አንዱ የጄኔራል መኮንኖቹን ማስሾም እንደሆነ ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል::

ሕወሀቶች የበላይነታቸውን እንደያዙ ለመቀጠል ያመቻቸው ዘንድ ባለፈው ሳምንት ውስጥ በየመስሪያ ቤታቸው እና በየቢሮዋቸው ምስጢራዊ ሰነዱ ለህወሀት አባሎች ብቻ የተሰጠ ሲሆን ከዚህም ሰነድ ውስጥ አንዱ ጦሩን በበላይነት በተጠናከረ መልኩ ለመቆጣጠር የሚል በመሆኑ የጄኔራል መኮንኖቹ ሹመት ድንገት ሊከናወን እንደቻለም ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በተለይ በጦሩ ውስጥ የአንድ ወገን የበላይነት ነግሶዋል በሚል ተቃውሞ በየአቅጣጫው እየተሰማ ባለበት በዚህ ግዜ የህወሀት ሰዎችን መልሶ በከፍተኛ ማዕረግ መሾም የሰራዊቱን አባላት ጥያቄ ውድቅ ማድረግና ሰራዊቱን መናቅ ነው የሚሉት የፖለቲካ ተንታኞች የማዕረግ ሹመት አሰጣሰጡ ያልታሰበበት እና ዱብ እዳ መሆኑም በግልጽ የታየ ሀቅ ነው ብለዋል::

አስገራሚው ነገር ይላሉ እነዚሁ የፖለቲካ ተንታኞች የእነ ስብሀት ነጋን ቡድን ለማጠናከር እና የህወሀትን የቀድሞውን የበላይነት መልሶ ለመቆጣጠር ሲባል ሰሞኑን በጥድፊያ ከተሾሙት ጄኔራሎች መሀከል በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ግዜ አንዲት የህወሀት በረሀ አመጣሽ ሴት የጄኔራል ማዕረግ የተሰጣት ሲሆን ከዚህ ቀደም በጦሩ አባላት የአንድ ወገን የበላይነት ነግሶዋል ይስተካከል እያሉ ጥያቄ ሲያቀርቡ ለነበሩት መኮንኖች እና አባሎች የንቀት መልስ የተሰጠበት መሆኑንም ጨምረው ገልፀዋል::

<u>ሰሞኑን ድንገት ከብ/ጄ/ልነት ወደ ሜጀር ጄኔራልነት ያደጉት መኮንኖች</u>

-ሜ/ጄ/ል መሐሪ ዘውዴ ገ/ማርያም-ህወሀት

-ሜ/ጄ/ል ሀሰን ኢብራሂም ሙሳ-ኦህዴድ

-ሜ/ጄ/ል መሰለ በለጠ አለሙ-ብአዴን ሲሆኑ

<u>ከኮሎኔል ወደ ብርጋዲየር ጄኔራልነት ማዕረግ የተሰጣቸው ደግሞ</u>

-ብ/ጄ/ል-ያይኔ ስዩም ገ/ማርያም-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-አታክልቲ በርሔ ገ/ማርያም-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ስብሀቱ በየነ ስዩም-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ገ/ኪዳን ገ/ማርያም የዕብይ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ጉዕሽ ፅጌ ወ/ገብርኤል -ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ማአሾ ሐጎስ ስዩም-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ገብሩ ገ/ሚካኤል ወልድ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል -መሸሻ ገ/ሚካኤል ኪ/ማርያም-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል -አብርሀ አረጋይ ለገስ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-አስካለ ብርሀነ (የመጀመሪያዋ ሴት ጄኔራል)-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ሐለፎም እጅጉ ሞገስ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል -አብርሐ ተስፋይ በርሔ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ሙሉ ግርማይ ገ/ህይወት-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ወ/ገብርኤል ባቢ ገ/መድህን -ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ፍስሐ ኪ/ማርያም ወ/ህይወት-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-ይብራህ ዘሪሁን ይህደጎ-ህወሀት

ብ/ጄ/ል -የማነ ሙሉ ሀፍተ-ህወሀት

-ብ/ጄ/ል-አሰፋ ገብሩ ወርቅነህ-ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ገ/መድህን ፍቃዱ ኃይሉ-ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ታረቀኝ ካሣሁን ብሩ -ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ይመር መኮንን ዓሊ-ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ዘውዱ በላይ ማለፊያ -ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ጥጋቡ ይልማ ወንድምአገኘሁ-ብአዴን

-ብ/ጄ/ል-ደግፌ ባዲ በጋዩ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-ኩምሳ ሻንቆ ደስታ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-አጫሉ ሸለመ መርጋ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-ሹማ አብደታ ሀካ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል -ድሪባ መኮንን ሀተኢ -ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-ከድር አራርሳ ይመር-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-ኩመራ ነገሪ ገመዳ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል-ዱባለ አብዲ ሁሉቃ-ኦህዴድ

-ብ/ጄ/ል -ደስታ አብቼ አገኖ-ደኢህዴን

-ብ/ጄ/ል-አሥራት ደነሮይ -ደኢህዴን

-ብ/ጄ/ል -አቤል አየለ ኢልቶ -ደኢህዴን መሆናቸው ታውቆዋል፡፡

በዚሁ ሰሞኑን በተደረገው የሹመት አሰጣጥ መሰረት 4 ሚሊዮን ህዝብ ብዛት ያለው የትግራይ ክልል -17 ጄኔራሎች፤25 ሚሊዮን ህዝብ ብዛት ያለው አማራ ክልል -6 ጄኔራሎች፤ከ30 ሚሊዮን በላይ ህዝብ ብዛት ያለው ኦሮሚያ-8 ጄኔራሎችን እንዲሁም ከ15 ሚሊዮን ህዝብ በላይ ያለው ደቡብ ክልል -3 ጄኔራሎችን በኮታ የተሾመላቸው መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ህወሀቶች በእነ ስብሀት ነጋ ግፊት አድራጊነት በአባይ ጸሀዬ ፊት ለፊት ተፋላሚነት የበላይነታቸውን ለመቆጣጠር እያሴሩ ባለበት ወቅት ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኃይለማርያም ደሳለኝ እና ከፕሬዝዳንቱ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ እውቅና ውጭ በህወሀቱ ጄኔራል ሳሞራ የኑስ እንዲሾሙ የተደረገ ቢሆንም በየጦሩ ክፍል ውስጥ ባሉ መኮንኖች እና የጦሩ አባሎች ህገ መንግስቱን ማስከበር..... ሀገርና ህዝብን ከውጭ ወራሪ መጠበቅ እንጂ ለጥቂት ቡድኖች አጎብዳጅ አንሆንም በማለት የተቃውሞ ጥያቄ ለአለቆቻቸው እያቀረቡ መሆኑም ሌላው የወያኔ የራስ ምታት እንደሆነ ተጠቁሞዋል፡፡

የጄኔራል መኮንኖቹ ሹመት አሁንም በአንድ ብሔር የበላይነት ላይ በማተኮር የተከናወነ በመሆኑ ከፍተኛ ቅሬታ ያደረባቸው የጦሩ አባላት በየጦር ክፍላቸው ውስጥ ተቃውሞ እያሰሙ በመሆኑ የወያኔ ባለስልጣናትም በጭንቀት ተወጥረው እንደሚገኙ ተጠቁሞዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የህወሀቶቹ እነ አባይ ፀሐዬ ከሁሉም በላይ ብአዴንን አጥብቀው እንደፈሩና ጥቃታቸውም በብአዴን ባለስልጣናት ላይ መሆኑን ያጋለጡት ምንጮቹ በተለይ በበረከት ስምኦን የሚመራውን ቡድን ኤርትራዊ በመሆኑ ከኢሳያስ ጋር ሊያብር ስለሚችል ተጠንቀቁ እያሉ ውስጥ ውስጡን የማጥላላት ዘመቻ መክፈታቸውንም ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

የህወሀት ቡድንም የጠቅላይ ሚኒስትርነት ቦታውን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ላይ ታች ሲል የሰነበተ ቢሆንም ያልተሳካለት ከመሆኑም በተጨማሪ እርስ በርስ ደግሞ የውስጥ ክፍፍል እንደፈጠሩም የውስጥ አዋቂ ምንጮች ጥቆማ አጋልጠዋል፡፡

ሕወሀት በሚቀጥለው ሳምንት ውስጥ በሚያደርገው የተናጥል የማዕከላዊ ስብሰባ ላይ በተጉዋደሉ አባላቶች ምትክ ምርጫ የሚያከናውን ሲሆን በመለስ ምትክ ለሊቀመንበርነት ቀዳሚና ዋነኛ አድርገው የሚያቀርቡት አርከበ እቁባይን እንደነበር  የጠቆሙት ምንጮቹ ለዚህም ሰፊ ቅስቀሳና ዘመቻ ውስጥ ውስጡን መጀመራቸውን ምንጮቹ ጨምረው ገልጸዋል።

የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ በሁለት ተከፍሎ ሁለት ሰዎችን ለሊቀመንበርነት እጩ አድርጎ ለማቅረብ እየተፋለመ መሆኑን ያጋለጠው የምንጮቹ ጥቆማ የጤና ጥበቃው ሚኒስትር ቴዎድሮስ አድሀኖምን እና አርከበ እቁባይን የሚደግፍ በሚል መከፋፈላቸውን ምንጮቹ አብራርተዋል።

በህወሀት ውስጥ የተፈጠረው ቡድንተኝነት ተጠናክሮ የቀጠለ ከመሆኑም በላይ ዶ/ር ቴዎድሮስ አድሀኖምን ለህወሀት እና ለኢህአዴግ ሊቀመንበርነት ለማስመረጥ በህወሀት ውስጥ ብቸኛዋ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የሆነችውና የሙዋቹ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን ቀንደኛ ተዋናይ ስትሆን አርከበ እቁባይን ለማስመረጥ ከሚጥሩት መሀከል ደግሞ የቀድሞው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በአሁኑ ሰዓት የቻይና አምባሳደር የሆነው ስዩም መስፍን እና የቀድሞው የህወሀት ሊቀመንበር ስብሀት ነጋ ይገኙበት እንደነበር  ምንጮቹ አስረድተዋል።

አርከበ እቁባይን የህወሀት ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል እንዲሆን ከማስመረጥ አልፎ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እጩ አድርጎ ለማቅረብ እቅድ እንደነበራቸው የጠቆሙት ምንጮቹ አዜብ መስፍን በበኩልዋ አንጋፋ  የህወሀት ሰዎችን እያሰባሰበች በዙሪያዋ እያሰለፈች ዶ/ር ቴዎድሮስን ለስልጣን ለማብቃት ስትታተር መክረምዋን ምንጮቹ ገልፀዋል።

የህወሀትን ጨምሮ አራቱ የወያኔ ድርጅት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ተጠናቅቆ እንዳለቀ የኢህአዴግ ማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ መስከረም አጋማሽ ላይ ይደረጋል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም ባልታወቀ ሁኔታ የወያኔ ማዕከላዊ ኮሚቴ ለሁለት ቀናት አስቸኩዋይ እና ድንገተኛ ስብሰባ አድርጎዋል።

አራቱ የወያኔ ድርጅቶች በተናጠል በየክልላቸው ርዕሰ መዲና ስብሰባቸውን ያከናውናሉ...... አቁዋሞቻቸውን ይፋ ያደርጋሉ...... ተብሎ ቢጠበቅም ለግዜው ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ ስብሰባው ሳይደረግ ቀርቶ መስከረም አጋማሽ ላይ ይከናወናል የተባለው የወያኔ ማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ ድንገት ዓርብ መስከረም **4** እና ቅዳሜ መስከረም **5** ቀን **2005** ዓ.ም ለሁለት ቀናት መደረጉ ታውቆዋል።

ይሄንኑ አስቸኩዋይ ስብሰባ በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ያደረገው **180** አባላት ያሉት የወያኔ ማዕከላዊ ምክር ቤት ስብሰባ ከሁሉም በፊት ሊቃነ መናብርቶችን መርጦ መሰየም ሲገባው በመሀከላቸው በተፈጠረው ትርምስ መግባባት ተስኖዋቸው ምርጫው ሳይደረግ ከአራቱም ድርጅቶች አንድ አንድ ሰው ተወክሎ ሁለት ቀናት የቆየ ስብሰባ ሲያደርግ የቆየ ሲሆን በዚሁ በግለሰቦች መከከል ንትርኮች ተነስተው እንደነበረ ማወቅ ተችሏል።

ከሊቀመንበር እና ምክትል ሊቀመንበር ምርጫ በተጨማሪ ከዚህ ቀደም ፓርቲው የአመራር ግንባታ ወይም መተካካት በሚል ባወጣው መመሪያ መሰረት ተፈጻሚ እንዲሆን በረከት ስምኦን አጥብቆ ቢጠይቅም የህወሀቱ አባይ ጸሀዬ ግን በአሁኑ ሰዓት አዳዲስ ካድሬዎች ወደ ስልጣን ቢመጡ

የጀመርነውን እቅድ ያፋልስብናል በማለት ግትር አቋዋም በመያዝ ሲወዛገቡ የሰነበቱ ሲሆን የሁለቱን ውዝግብ እና ንትርክ ለማርገብ ሲል አዲሱ ለገሰ መሀል ሰፋሪ የሆነ አቋዋም በመያዝ እዚያና እዚህ እያለ ሲዋልል መደመጡንም ይሄው ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል::

በረከት ስምኦን መለስ ከመሞቱ አስቀድሞ ወጣት ካድሬዎችን እያደራጀ ወደ ክልሎች አስርጎ ማስገባቱን መግለጻችን የሚታወስ ሲሆን ይህንኑ የተረዳው የህወሀቱ አባይ ጸሐዬ ገና ለገና የአፍለኛ ከተሜ ካድሬዎችን ድጋፍ ይነጥቀናል በሚል ስጋት የተነሳ በረከት በስብሰባው ላይ ያነሳውን የመተካካት ሀሳብ ውድቅ በማድረግ እያጣጣለ ያቀረበ ከመሆኑም በላይ እስከ ዛሬ ድረስ በአደባባይ እና በወያኔ ከፍተኛ ባለስልጣናት ፊት ታይቶ ያልታወቀ ፈሩን የለቀቀ ንግግር ከማድረጉም በተጨማሪ እንደ አለቃው መለስ ጠረጴዛ እየቀጠቀጠ ደማችንን ያፈሰስነው.....አጥንታችንን የከሰከስነው.....አካለ ጎዶሎ የሆንነው......የወጣትነት እድሜያችንን የጨረስነው......ለከተማ አውደልዳይ አይደለም በማለት እግረ መንገዱን የስልጣን ተቀናቃኝ የሆነበትን ኃይለማርያም ደሳለኝን እና ሌሎች ከተማ አፈራሽ ባለስልጣናትን ጭምር ሲሳደብ እንደነበር ከቤተ መንግስት ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል:

በአባይ ጸሐዬ አነጋገር የተበሳጩ የምክር ቤቱ አባላት እጅ እያወጡ የበኩላቸውን ሀሳብ ለመስጠት ቢሞክሩም የወቅቱ መድረክ መሪው ኃይለማርያም ደሳለኝ ሁኔታው እንዲበርድ እድሉን ሳይሰጥ ለሻይ እረፍት በሚል ስበሰባውን እንዳቋዋረጥና ሲመለሱም ወደ ሌላ አጀንዳ እንዲዞር ማድረጉን ይሄው ሾልኮ የደረሰን ጥቆማ አመልክቶዋል::

በተለይ ዓርብ መስከረም 4 ቀን 2005 ዓ.ም ስብሰባው በተጀመረበት ወቅት የነበረው የቃላት ጦርነት አስፈሪና አስደንጋጭ እንደነበር ጥቆማው አጋልጦዋል:: ባልዋን ድንገት ያጣችው አዜብ መስፍን ሳይቀር በቃላት ጦርነቱ ውስጥ ተሳታፊ እንደነበረችም ይሄው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶ በምርጫው ላይ መግባባት በመጥፋቱ ከአራቱም ድርጅቶች አንዳንድ ተወክለው ስብሰባውን እንዲመሩ ከመደረጉም በተጨማሪ አዲስ አደረጃጀት ማከናወናቸውም ታውቆዋል::

በዚሁ በተደረገው አዲስ አወቃቀር ላይ ህወሀቶች የኢህአዴግን ሊቀመንበርነቱን ስልጣን ለመንጠቅ ቢያስቡም ቤቱ በአንድ ድምጽ ውድቅ በማድረጉ ነገር ግን ደግሞ የነሱንም ጥያቄ ጨርሶ ላለመጣል ሲባል እስከ ዛሬ አንድ ምክትል ሊቀመንበር የነበረው አደረጃጀት ተለውጦ ሶስት እንዲሆን ተደርጎዋል ተብሎዋል::

የሊቀመንበርነቱን ቦታ ኃይለማርያም ደሳለኝ የተቆጣጠረ ሲሆን ደመቀ መኮንንመ ምክትል ሊቀመንብር መሆኑም ታውቆዋል::

መለስ ዜናዊ የሀገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ....የህወሀት ሊቀመንበር...የኢህአዴግ ሊቀመንበር.....የጦር ኃይሎች ዋና አዛዥ.....የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሊቀመንበር..... የፌዴራል ፖሊስ የበላይ ተጠሪ..... የጸረ ሙስና የበላይ ጠባቂ......የሚሉና ሌሎች እጅግ ብዙ ስልጣኖችን ጠቅልሎ ይዞ ለ21 ዓመታት የዘለቀ ሲሆን ዛሬ ከደቡብ የተገኘው ኃይለማርያም ይሄንን ሁሉ ስልጣን ሊይዝ ይችላል ወይ የሚል ጥያቄ ሁሉም እየጠየቀ ያለበት ነው::

በተያያዘ ዜና በመለስ ዜናዊ ምትክ ለቦታው የሚመጥን ሰው ወደ ስልጣን ለማምጣት ከሀገሪቱ ህገ መንግስት አንጻር ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝ በተጨማሪ የኢህአዴግ ማዕከላዊ ኮሚቲ አባሎች እና የተወካዮች ምክር ቤት አባል ከሆኑት መሀከል የመንግስት ጉዳዮች ኮሙኒኬሽን ሚኒስትር በረከት ስምኦን.....የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ዶ/ር ቲዎድሮስ አድህኖም......የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ  አባዱላ ገመዳ ......አዜብ መስፍን.....አርከበ እቁባይ የተሻለ እድል አላቸው ተብሎ ሲናፈስ የሰነበተው ወሬ መና መቅረቱ ተጠቆመ::

ህገ መንግስቱ ካልተቀየረ በስተቀር ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እንደማይወዳደሩ እየታወቀ በመለስ ዙሪያ የነበሩና ለረዥም ዓመታት አብረው ሲሰሩ የነበሩት አምባሳደር ስዩም መስፍን ......አምባሳደር ብርሀነ ገብረክርስቶስ......አቶ ጸጋዬ በርሔ....አምባሳደር ግርማ ብሩ ......አቶ አዲሱ ለገሰ .....የስራ ልምዱ አላቸው .....ብቁ ናቸው... እያሉ በነ ስብሀት ነጋ ቡድን ሰፊ የማሳሳቻ ዘመቻ ሲያደርጉ እንደነበረም ታውቆዋል::

በሌላ ዜና በወያኔ ባለስልጣናት መሀከል የከረረ ጥላቻና ቡድንተኝነት ተስፋፍቶ ባለበት በዚህ ወቅት የትግራይ ክልል ርዕሰ መስተዳድር የሆነው አባይ ወልዱ ለትግራይ ህዝብ አዲስ የትግል ጥሪ ማቅረቡ በወያኔ ቡድን ውስጥ ከፍተኛ ክፍተት መፈጠሩን በይፋ ያመላከተ መሆኑ ተነገረ::

የአዲስ ዓመት ዘመን መለወጫን ምክንያት በማድረግ ባስተላለፈው መልዕክት የጀመርነውን ትግል ከዳር ሳናደርስ መስመራችንን ሊያስቱ የሚችሉ ኃይሎች ብቅ ብቅ እያሉ በመሆኑ  የትግራይ ህዝብ እንደ ከዚህ ቀደሙ ከጎናችን እንዲሰለፍ ሲል ጥሪ ማቅረቡ አስገራሚና አስደማሚ ንግግር ማድረጉ ታውቋል::

በትግራይ ህዝብ ላይ ለ21 ዓመታት የቁም አሳሩን ሲያሳዩትና ሲጫወቱበት የኖሩት እነዚሁ የህወሀት ባለስልጣናት ዛሬ በወያኔ ቡድን ውስጥ በተፈጠረው ክፍፍል እና ቡድንተኝነት በድምጽ ብልጫ እንደሚሸነፉ በማወቃቸው ብቻ መላውን የትግራይ ህዝብ ከጎናቸው ለማሰለፍ ሲሉ የድረሱልን ጥሪ ማቅረባቸው በእጅጉ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር መሆኑን የትግራይ ተወላጆች ሲናገሩ ተደምጠዋል::

በትግራይና በመላ ኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ለ21 ዓመታት በጫንቃው ላይ ሲያናጥሩ ኖረው ዛሬ እርስ በርስ በፈጠሩት የስልጣን ሽኩቻ ሳይስማሙ በመቅረታቸው እና ሜዳው ገደል ሲሆንባቸው ተዋድዶ የኖረውን ህዝብ ዳግም ለመነጣጠል ለትግራይ ሕዝብ ብቻ የድረሱልን ጥሪ ቢያቀርቡም አድማጭ እና ሰሚ አጥተው አንገታቸውን መድፋታቸውንም ከትግራይ የደረሰን  ዘገባ ገልጾዋል::

በተለይ ይሄው ነባር የበረሀ ታጋይ የሆነው የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር አባይ ወልዱ የተባለው ግለሰብ ባስተላለፈው ጥሪ መሰረት እራሱን የውጭ ሀገር ዜጋ አድርጎ የትግራይን ህዝብ ከተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ጋር ተነጥሎ ያለ በማስመሰል ያቀረበው ጥሪ ህወሀቶች ዛሬም በህዝቡ መሀከል ሊቀብሩት የሚፈልጉት የጥፋት ፈንጂ መኖሩን የሚያመላክት ነው ተብሎዋል::

የትግራይ ህዝብ በችግር እና በችጋር ......የሚላስ የሚቀመስ አጥቶ ህይወቱን ለማቆየት ቀዬውን ለቅቆ ወደ መሀል ሀገር ወዳለው ወገኑ እየተሰደደ መሆኑን የሚያውቁት የህወሀት ባለስልጣናት አንድም ግዜ መፍትሄ ሳይሰጡ ኖረው ዛሬ በመሀከላቸው በተነሳ መከፋፈል ስልጣን ሊያጡ መሆኑን ሲያውቁ ህዝቡን ድረስልን እያሉ መወትወታቸው እና ከወገኑ ጋር ሊያጋጩት ጥረት ማድረጋቸው አሳፋሪ ተግባር ነው ሲሉ የትግራይ ተወላጆች በቁጭት ሲናገሩ ተደምጠዋል።